# የዓለም አቀፍ ተባባሪዎች ቅኝት ሪፖርት



music as therapy international

# አመሰግናለሁ

‘*Music as Therapy International*’ ያለውን ሙዚቃን ለተጋላጭ ህፃናት እና አዋቂ ደህንነት የመጠቀም ራዕይ ለማሳካት እንደ እርስዎ ያሉ ዓለም አቀፍ ተባባሪ እጅግ በጣም አስፈላጊ ናቸው። ‘*Music as Therapy International*’ ስልጠናን እና ድጋፍን ለመስጠት ቢችልም ሙዚቃን እንደ ቴራፒ ማዳረስ የሚችሉት ተባባሪዎቻችን ናቸው። የማዳረስ አቅምን ለማበረታታት ደግሞ እኛ ሁሌም ቢሆን በተቻለ መጠን በተባባሪዎቻችን ሥራ እና በሚያገለግልዋቸው ህፃናት እና አዋቂዎች ላይ የሙዚቃ ቴራፒ ምን አይነት ጠቀሜታ እንዳለው መገንዘብ እንፈልጋለን። በ 2019/20 ተባባሪዎቻችንን ይህንን ጠቀሜታ እና ስለ ሥራቸውም እንዲገልፁልን ቅኝት እንዲያሟሉልን መጠየቃችን ይታወሳል። ቅኝቱን አሟልተው ለመለሱልን ተባባሪዎቻችን ምስጋናችንን ማቅረብ እንፈልጋለን!

72 ተባባሪዎች ከ56 የእርዳታ ማዕከላት እና ከ7 ሀገራት በቅኝታችን ላይ ተሳትፈዋል። መልሰቻቸውም ለእኛ እጅግ በጣም ጠቃሚ እና አበረታታች ናቸው። ሁሉም ተባባሪዎቻችን በቅኝቱ ላይ ባይሳተፉም፣ ይህን ሪፖርት ትክክለኛ እና አማካይ ለማድረግ የተሳታፊዎቹ ቁጥር በቂ ነው ብለን እናምናለን። ሪፖርቱን ስታነቡት ደስ እንደሚላችሁ ተስፋ እያደረግን ምንም አይነት ጥያቄ ወይንም አስተያየት ካላችሁ እንድትልኩልን እንጋብዛለን።

# የዓለም አቅፍ ትባባሪዎች ማጠቃለያ



music as therapy international

# የዓለም አቅፍ ትብባሪዎች ማጠቃለያ

*'Music as Therapy International'* ከ1998 ጀምሮ እስከ 2021 ድረስ ከተባባሪዎች ጋር ሲሠራ ኖሯል።እኚህ ተባባሪዎችም ሙዚቃን አሁንም በመጠቀም ላይ ናቸው። በአማካዩ የዓለም አቀፍ ተባባሪዎቻችን ሙዚቃን ለ7 ዓመታት ተጠቅመዋል።

አንድ አንዶቹ ተባባሪዎቻችን የሙዚቃ ክፍለ ጊዜን የመጀመሪያው የመግቢያ ስልጠና በተደረገበት ቦታ ላይ አሁንም እያከናወኑ ይገኛሉ፤ ሌሎችም በሌላ ቦታ ላይ ወይንም እራሳቸው ባቋቋሙት ቦታ ላይ እያከናወኑ ይገኛሉ።

## ዓለም አቀፍ ተባባሪዎቻችን




ቅኝታችንን አሟልተው የመለሱልን ተባባሪዎቻችን በ56 የእርዳታ ማዕከላት ላይ እየሠሩ ይገኛሉ።




እነርሱም ለ9,868 እርዳታ የሚፈልጉ ሰዎች የሙዚቃ ክፍለ ጊዜን ማዳረስ ችለዋል።

ከዚህ ስር የሚገኘው ካርታ ቅኝቱን ያሟሉ ተባባሪዎቻችን የት እንደሚገኙ ያሳያል።




## ተባባሪዎቻችን ጋር እርዳታ የሚያገኙ ተጠቃሚዎች

ከዚህ ስር የሚገኘው ፓይ ቻርት የተባባሪዎቻችንን የሙዚቃ ክፍለ ጊዜ ተጠቃሚ የሆኑትን ሰዎች በእድሜ አከፋፍሎ ያሳያል።






የሚበዙት ተባባሪዎቻችን ሙዚቃን ከመግባባት፣ ከቋቁቋ፣ ከትምህርት እና ከሃይፐራክቲቪቲ ጋር ችግር ላላቸው ልጆች እና አዋቂዎች ለመርዳት እየተቀሙ ይገኛሉ።

## የሙዚቃ ክፍለ ጊዜ

ቅኝቱን ካሟሉት ተባባሪዎቻችን 67% የሚሆኑት ሙዚቃን በመደበኛነት ይጠቀማሉ። 92% የሚሆኑት የሥራ ባልደረቦቻቸውን ሙዚቃን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል አሳይተዋል፤ 83% የሚሆኑትም ስለ ሙዚቃ ጠቀሜታ ከባልደረቦቻቸውም እና ከሌሎችም ጋር እንደሚወያዩ ገልጸዋል።

በቀኝ በኩል ያለው ቬን ዳያግራም ከተባባሪዎቻችን መካከል ስንቶቹ ሙዚቃን እንደሚጠቀሙ ለይቶ ያሳያል።




በግራ በኩል ያለው ፓይ ቻርት ደግሞ ተባባሪዎቻችን ሙዚቃን ምን ያህል እንደሚጠቀሙ ይገልጻል።

## የመግቢያ ስልጠና ፕሮጄክት ተጽዕኖ

የመግቢያ ስልጠና ፕሮጄክት ጀምሮ፥

ከተባባሪዎቻችን 99% የሚሆኑት በመግቢያ ስልጠና ፕሮጄክቱ የተማሩት ነገር በሥራቸው፤ በአስተማሪነታቸው እና እንክብካቤን በሚሰጡበት ዘዴ ላይ ለውጥ አምጥቷል ይላሉ።

92% የሚሆኑትም የተማሩት ነገር ከሙዚቃ ክፍለ ጊዜም አልፎ እንደጠቀማቸው ይናገራሉ።

ከተባባሪዎቻችን 97% በሙዚቃ ክፍለ ጊዜ ኩራት ይሰማቸዋል።

94% የሚሆኑትም ልበ ሙሉነትን እንደ ጨመረላቸው አሳውቀውናል።

90% ኃላፊነትን እንደጨመረላቸው ተናግረዋል።

92% የሚሆኑትም ለሥራቸው ያላቸውን ቁርጠኝነት እንደጨመረላቸው ይናገራሉ።

## የተባባሪዎቻችን የሙዚቃ ክፍለ ጊዜ ተጽዕኖ

ተባባሪዎቻችን ከሚንከባከቧቸው ሰዎች 89% የሚሆኑት ከሙዚቃ ክፍለ ጊዜው ጥሩ ተጠቃሚ እንደሆኑ አሳውቀውናል። አብዛኛዎቹ ተባባሪዎቻችን ለሙዚቃ ከፍተኛ የሕክምና ጥቅሞች እንዳሉ አስተውለዋል።

እነዚህም የሚከተሉት ናቸው - መደሰት፤ተሳትፎን መጨመር፤ ስሜትን መግለፅ፤ ትኩረትን ማበረታታት እና ጭንቀትን መቀነስ።

## ከ'*Music as Therapy International*' ጋር መሥራት

ከተባባሪዎቻችን 86% የሚሆኑት የመግቢያ ስልጠናው ላይ ለመሳተፍ ቀላል እንደነበር ገልጸዋል።

92% የሚሆኑትም በመሳተፋቸው ደስተኛ እንደሆኑ ነግረውናል።

92% የሚሆኑትም ስልጠናውን የሰጣቸው የሙዚቃ ቴራፒስት በቂ ሙያ እና ዕውቅና እንደነበረው/እንደነበራት ይናገራሉ።

89% ከ'*Music as Therapy International*' ቀጣይ ድጋፍ አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል።

ከዓለም አቀፍ ተባባሪዎቻችን 96% የሚሆኑት የ'*Music as Therapy International*' ስልጠናን ሌሎችም እንዲጠቀሙበት ይመክራሉ።


ኢትዮጵያ
music as therapy
international

# ኢትዮጵያ

'Music as Therapy International' በኢትዮጵያ ውስጥ ከ2018 ጀምሮ ሥራውን ሲያከናውን ኖሯል። ኢትዮጵያዊ ተባባሪዎቻችን በጣም ሰፊ ከሆኑ የደንበኛ ቡድኖች ጋር ይሠራሉ እና ከሌሎች ሀገሮች በተቃራኒው ዕድሜያቸው ከ 26+ ዓመት ከሆኑ ጎልማሶች ጋር በዋናነት እየሠሩ ይገኛሉ።

## ተፅዕኖ




ኢትዮጵያዊ ተባባሪዎቻችን በ3 የእንክብካቤ ማዕከላት ላይ ይሠራሉ። እነዚህም የመግቢያ ስልጠናው የተከናወነባቸው ቦታዎች ናቸው።




በአጠቃላይ 612 አዋቂዎች የሙዚቃ ክፍለ ጊዜን በነዚህ ቦታዎች ላይ ለመጠቀም እድሉን አግኝተዋል።

## ተባባሪዎቻችን ጋር እርዳታ የሚያገኙ ተጠቃሚዎች




በግራ በኩል ያለው ፓይ ቻርት በሙዚቃ ዝግጅቶች ውስጥ የሚሳተፉ ተጋላጭ ሰዎችን የዕድሜ ቡድኖችን ይወክላል።

በቀኝ በኩል ያለው ባር ቻርት ሙዚቃን የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸው ሰፊ ተጋላጭ ሰዎችን ለመርዳት የሚጠቀሙትን የኢትዮጵያ አጋሮቻችንን መቶኛ ያሳያል።




## የሙዚቃ ክፍለ ጊዜ

ኢትዮጵያዊ ተባባሪዎቻችን የሙዚቃ ዝግጅቶቻቸው ለሥራቸው አስፈላጊ አካል መሆናቸውን አመልክተዋል።

ቅኝቱን ከመለሱት 67% የኢትዮጵያ አጋሮቻችን አሁንም ሙዚቃን እየተጠቀሙ ሲሆን 33% ደግሞ የሙዚቃ ክፍለ ጊዜዎችን አቋርጠዋል።

ሁሉም ኢትዮጵያዊያ ተባባሪዎቻችን በሚሠሩበት የእንክብካቤ ማዕከል ላይ በሳምንት ከአንድ ጊዜ በላይ የሙዚቃ ክፍለ ጊዜዎችን እንደሚያቀርብ ነግረውናል፤ እና ለአንዱ ማዕከል ሙዚቃን በየቀኑ እንደሚጠቀም ተገንዝበናል።

100% ኢትዮጵያዊ ተባባሪዎቻችን ሙዚቃን እንዴት እንደሚጠቀሙ ለባልደረቦቻቸው እና ለሌሎችም አሳይተዋል።

የሙዚቃ ክፍለ-ጊዜዎችን ከሚሰጡ የእንክብካቤ ማዕከላት መካከል 33% የሚሆኑት አጋሮች ከግለሰቦች ጋር የሚሰጡት ሲሆን 67% የሚሆኑት የቡድን ስብሰባዎችን እያካሄዱ ነው።

## የመግቢያ ስልጠና ፕሮጄክት ተጽዕኖ

የመግቢያ ስልጠና ፕሮጄክት ጀምሮ፥

of ከተባባሪዎቻችን 100% የሚሆኑት በመግቢያ ስልጠና ፕሮጀክቱ የተማሩት ነገር በሥራቸው፤ በአስተማሪነታቸው እና እንክብካቤን በሚሰጡበት ዘዴ ላይ ለውጥ አምጥቷል ይላሉ።

100% የሚሆኑትም የተማሩት ነገር ከሙዚቃ ክፍለ ጊዜም አልፎ እንደጠቀማቸው ይናገራሉ።

ከተባባሪዎቻችን 100% በሙዚቃ ክፍለ ጊዜ ኩራት ይሰማቸዋል።

100% የሚሆኑትም ልበ ሙሉነትን እንደ ጨመረላቸው አሳውቀውናል።

100% ኃላፊነትን እንደጨመረላቸው ተናግረዋል።


100% የሚሆኑትም ለሥራቸው ያላቸውን ቁርጠኝነት እንደጨመረላቸው ይናገራሉ።

*"በማንኛውም ሌላ ሥራ ሲሳተፉ ደስታ የማይሰማቸው ግን ሙዚቃን ብቻ የሚወዱ ተማሪዎች አሉ።"*

*(ፍቅር የኢትዮጵያ አእምሮ እድገት ውስንነት ብሔራዊ ማሕበር፣ 2020)*

## የተባባሪዎች የሙዚቃ ክፍለ ጊዜ ተፅዕኖ

ከዚህ በታች ያለው ባር ቻርት በእንክብካቤ ስር ያሉ ተጋላጭ የሆኑ ሰዎች ከሙዚቃ ስብሰባዎቻቸው የሕክምና ጥቅሞች እያገኙ ነው የሚሉትን ተብባሪዎች መቶኛ ያሳያል።




## ከ'*Music as Therapy International*' ጋር መሥራት

ከኢትዮጵያዊ ተባባሪዎቻችን 67% የሚሆኑት የመግቢያ ስልጠናው ላይ ለመሳተፍ ቀላል እንደነበር ገልጸዋል።

33% የ'*Music as Therapy International*' መግቢያ ስልጠና የእነርሱን ፍላጎት እንዳሟላ ተናግረዋል።

100% በመሳተፋቸው ደስተኛ እንደሆኑ ነግረውናል።

100% የሚሆኑትም ስልጠናውን የሰጣቸው የሙዚቃ ቴራፒስት በቂ ዕውቅና እንደነበረው/እንደነበራት ይናገራሉ፤ 67% የሚሆኑትምስልጠናውን የሰጣቸው የሙዚቃ ቴራፒስት በቂ ሙያ እንደነበረው/እንደነበራት ገልጸዋል።

100% የስልጠናው ጠቀሜታ ከጠበቁት በላይ እንደነበረ እና ሌሎችም እንዲሳተፉበት እንደሚመክሩ ትናግረዋል።

67% ከ'*Music as Therapy International*' በቂ መረጃ እንደሚያገኙ ገልጸዋል።

100% ከ'*Music as Therapy International*' ቀጣይ ድጋፍ አስፈላጊ እንደሆነ ተናግረዋል።

# ቁልፍ ትምህርቶች

ሙዚቃ በዓለም ዙሪያ ላይ ያሉ አጋሮቻችን ለሚሰጡት እንክብካቤ በጣም አስፈላጊ አካል ሆኖ ቀጥሏል። ከተጠናቀቁ የዳሰሳ ጥናቶች ለወደፊቱ የመግቢያ ስልጠናን ለማሻሻል እና አካባቢያዊ ልምዶችን ለመገንዘብ የሚያስችሉ ሌሎች ብዙ ቁልፍ ትምህርቶች አሉ።

**የሙዚቃ ቴራፒቲካዊ ጥቅሞች፥** አጋሮቻችን ሙዚቃ በእንክብካቤያቸው ስር ላሉት ተጋላጭ ሰዎች አዎንታዊ እና ትርጉም ያላቸው ልምዶችን እንደሚሰጥ፤ ዕድሎችን ከፍ እንደሚያደርግ እና የተለያዩ ችግሮች ለሚያጋጥሟቸው ሰዎች ሊኖረው የሚችለው ከፍተኛ ተጽዕኖን ይገልጻሉ። ብዙዎች በግላቸው እንዴት እንደሚጠቀሙም ነግረውናል። የሙዚቃ አጠቃቀም ከአንዳንዶቹ የተጋላጭ ሰዎች ቤተሰቦች ጋር የሚያደርጉትን ስራ እንዴት እንዳጠናከረላቸውም አሳውቀውናል። ከሀገር ወደ ሀገር አጋሮቻችን የሚያገለግሉት አይነት ሰው እና ዋና ትኩረት የሚያደርጉበት ግጽታ ቢለያይም በመላው ዓለም አውታረ መረባችን ላይ ጋራነት አለ።

**ዘላቂ ተጽዕኖ፥** በ'*Music as Therapy International*' የተሰጠውን የመግቢያ ሥልጠና ተከትሎ የእኛ ዓለም አቀፍ ተባባሪዎች አዳዲስ የሙዚቃ ችሎታዎችን ከሥራዎቻቸው ጋር ማዋሃድ ይችላሉ። ቀጣይነት ባለው ድጋፍ፣ ይህ የሙዚቃ አጠቃቀም ወደ እንክብካቤ እና ትምህርት ሊገባ እና ለርዥም ጊዜ ሊቆይ ይችላል።

**የአቅም ማጠናከሪያ፥** ብዙ አጋሮቻችን የሙዚቃ ስልጠናው እንዴት ሙያቸውን ማሳደግ፤ ማዳበር እና ማሻሻል እንዳስቻላቸው ነግረውናል። የግል አመራርም ጠንካራ ነው። ብዙ አጋሮች በበርካታ የተለያዩ ሀገሮች ክህሎቶቻቸውን ለሌሎች በማካፈል እና ሙዚቃ በአካባቢያቸው ያለውን የህክምና ሚና ከፍ እያደረጉ ይገኛሉ።

**የባልደረባዎቻችንን ፍላጎት ማዳመጥ፥** እያንዳንዱ የፕሮጀክት ደረጃ ልማት የሚካሄድበት አካባቢ የሚፈለገውን ነገር ላማሟላት በባልደረባ እንድንመራ እንተጋለን። ሆኖም፣የባልደረባ ግብረመልስ እኚህ በአካባቢያዊ ደረጃ የሚፈለጉት ነገሮች ሁልጊዜ  እንደማይሰሙ ያሳያል። የሁሉንም ተባባሪዎቻችን ድምፅ እና አስተያየት ለማካተት እና በእኛ በኩል ያሉትን እጥረቶች ለመረዳት የበለጠ መሥራት ይኖርብናል።

**ድጋፋችንን ለይቶ መስጠት፥** አጋሮቻችን የሙዚቃ ልምምድን በተመለከተ ተጨማሪ እገዛ የሚፈልጉባቸውን ገጽታዎች አስተላልፈውልናል።  እኚህም፥

- የሙዚቃ ሥራ እንዲከናወን እና እንዲሻሻል የሚያስችሉ እቃዎችን ማቅርብ። በተለይ ለአእምሮ ህመምተኞች እና በአሰቃቂ ሁኔታ ለሚኖሩ ሰዎች።
- በ'*Music as Therapy International*' ዓለም አቀፍ አውታረ መረብ ላይ ተባባሪዎቻችን ከሙዚቃ ጋር ተያይዞ ያገኙትን ልምድ እና ጠቀሜታ እንዲያስትላልፉ ማመቻቸት።
- የአጋሮቻችን ሙዚቃ ክፍለ-ጊዜዎች ላይ የክትትል መዳረሻ ማመቻቸት።
- ተባባሪዎቻችን የሙዚቃ አጠቃቀማቸውን እንዲያስፋፉ እና እንዲያሻሽሉ ማድረግ።
- ሥራቸውን እንዲቀጥሉ እና እንዲያሻሽሉ አዳዲስ ወይንም ተጨማሪ የሙዚቃ መሳሪያዎችን ማቅረብ።

**ተሳትፎ፥** የኮቪድ-19 ተግዳሮቶች ቢኖሩም በቅኝታችን ላይ ዝርዝር ምላሾችን ባቀረቡት ተባባሪዎች ቁጥር ተደስተናል። ታሪካቸውን ለማካፈል እና ትምህርታቸውን ለመቀጠል ያላቸው ፈቃደኝነት በሙዚቃ የሚሰጡትን እንክብካቤ ለመቀጠል ያላቸውን ጠንካራ ቁርጠኝነትን ያሳያል።የአጋሮቻችንን የሙዚቃ አጠቃቀም ለማሳደግ የምንችልባቸውን አዳዲስ መንገዶች እና ዘዴዎችን አግኝተናልና ወደፊት የሚኖረንን ሥራ ለማከናወን ዝግጁ እና ደስተኛ ነን።



Music as Therapy International
Mowll Street Business Centre
11 Mowll Street
London SW9 6BG

music as therapy international

Tel. +44 (0) 20 7735 3231
Email: info@musicastherapy.org
Skype: mastinternational